የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 6/0281/13
ቀን/Date መጋቢት 08 2013

**ለየጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**
**ባሉበት**

**ጉዳዩ፡- የፀደቀ የትራንሽፕመንት የአሰራር ስርዓት መላክን ይመለከታል፡፡**

የጉምሩክ ትራንሽፕመንት አሰራር ስርዓት አስመልክቶ ከዘርፉ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የአየር መንገድ እና የተለያዩ ክፍሎች የሰጡትን ግብዓት ከጽ/ቤት ባለሙያ ጋር በጋራ በማየት በትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀውን የአሰራር ስርዓት በዘርፍ በኩል በዝርዝር ታይቶና ዳብሮ ወደ ተግባር ስርዓት ለመግባት ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀው የአሰራር ስርዓት እንዲጸድቅ በቀን 24/6/2013 ዓ.ም. በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ ለክቡር ኮሚሽነር ቀርቦ በቀረበው አሰራርና የውሳኔ ሀሳብ መሠረት ተፈፃሚ እንዲደረግ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

ስለሆነም የጸደቀው የትራንሽፕመንት የአሰራር ስርዓት በጥንቃቄ እና በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳወኩ፤ ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የፀደቀውን የትራንሽፕመንት የአሰራር ስርዓት 14 ገጽ ኮፒ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዘለው ጫኔ አበበ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን
ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

እንዲያውቁት/
- ለክቡር የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ/
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  ጉምሩክ ኮሚሽን



ስልክ/Tel:- +251 116 62 98 00
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: customscommission@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጉምሩክ ኮሚሽን

F.D.R.E. CUSTOMS COMMISSION

የውስጥ መፃፃፊያ

# INTERNAL OFFICE MEMORANDUM

ቁጥር፡ ጉኦዘ/6/370/13

**ለ፡ ክቡር የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር**

**ከ፡ ጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ**

**ቀን፡ 24/6/2013 ዓ.ም.**

**ጉዳዩ፡- የትራንሽፐመንት የአሰራር ስርዓት ስለማቅረብ፤**

የጉምሩክ ትራንሽፐመንት አሰራር ስርዓትን አስመልክቶ ከዘርፉ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የአየር መንገድ እና የተለያዩ ክፍሎች የሰጡትን ግብዓት ከጽ/ቤት ባለሙያ ጋር በጋራ በማየት የተጠናቀቀ የአሰራር ስርዓት ለትግበራ እንዲውል የትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በቀን 20/6/2013 ዓ.ም. በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ 12 ገጽ አባሪ አያይዘው አቅርበዋል፡፡

በመሆኑም የአሠራር ስርዓቱ በዘርፍ በኩል በዝርዝር ታይቶ የዳበረ የአሰራር ስርዓት ስለሆነ ወደ ተግባር ስራ ለመግባት ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀው የአሰራር ስርዓት እንዲጸድቅ የአሰራር ሰነዱን 13 ገጽ ኮፒ አባሪ አያይዘን ለውሳኔ አቅርበናል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጉምሩክ ኮሚሽን
**CUSTOMS COMISSION**
*የውስጥ ማስታወሻ*
*Inter Office Memorandum*

ለ፡ ጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ

ከ፡ ትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ቀን፡ 20/06/2013

ጉዳዩ፡- <u>የተጠናቀቀ የጉምሩክ ትራንሽፕመንት አሰራር መላክን ይመለከታል</u>

ቀደም ሲል በ24/03/2013 ዓ.ም በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ የአሰራር ስርዓቱን መላካችን ይታወቃል፡፡

ከዘርፍ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የአየር መንገድ እና የተለያዩ ክፍሎች የሰጡትን ግብዓት ከጽ/ቤት ባለሙያ ጋር በጋራ በማየት የተጠናቀቀ የአሰራር ስርዓት በዘርፍ በኩል ለትግበራ እንዲውል 12 ገፅ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

- ለመጋዘን አሠራርና ድጋፍ ቡድን

# በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
# Ethiopian Customs Commission

## የጉምሩክ ትራንሽፕመንት

## አሰራር ስርዓት

## (Customs Transhipment procedure)

### ትራንዚት እና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation

አዲስ አበባ

2013 ዓ.ም

ማውጫ                                                            ገፅ


ማውጫ ........................................ i

መግቢያ ........................................ 3

1. የአሰራር ስርዓቱ አላማ ........................................ 3

2. ትርጓሜ ........................................ 4

3. የጉምሩክ ትራንሽፐመንት አሰራር የህግ ማዕቀፎች ........................................ 4

4. የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ........................................ 5

5. ለጉምሩክ የትራንሽፐመንት ስራ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች ........................................ 5

6. የጉምሩክ ትራንሽፐመንት ስነ-ስርዓት አፈጻጸም ሂደቶች ........................................ 5

  6.1. ትርጉም ........................................ Error! Bookmark not defined.

  6.2. ቅድመ ሁኔታዎች ........................................ 5

  6.3. ዝርዝር የተግባር አፈፃፀም ደረጃዎች ........................................ 6

  6.4. የጊዜ አጠቃቀም ማጠቃለያ ........................................ 12



No.1
Ethiopia Customs Commission
Records Documentation

## መግቢያ

ማንኛውም ገቢ ዕቃዎች ወደ ሀገሪቱ የጉምሩክ የግዛት ክልል ሲገባ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መክፈል እንደሚጠበቅበት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ተደንግጓል፡፡ የትራንሸፐመንት ዕቃዎች በሀገሪቱ የጉምሩክ ግዛት ክልል ውስጥ በጉምሩክ ወደብ ወይም ጣቢያ ደርሰው ማጓጓዣ በመቀየር ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው ወደሆነው ሀገር በሚተላለፉበት ጊዜ ቀረጥና ታክስ መክፈል ሳይጠበቅባቸው እንዲሁም በጉምሩክ ወደቦች/ጣቢያዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የትራንዚት መጨናነቅ ለመቀነስ እና ተገቢ የጉምሩክ ቁጥጥር ለማድረግ ቀላል እና ውጤታማ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ የትራንስፖርት እና የሎጅስቲክስ አገልግሎት ካለው ተፈላጊነት አኳያ የተለያዩ ሀገራት አስመጭዎች እና ላኪዎች በደንበኝነት የያዘ ሲሆን ኢትዮጵያንም በአየር ለሚጓጓዙ ጭነቶች ማተላለፊያ እና ማሰራጫ ማዕክልነት (Hub) ተመራጭ ሃገር እየሆነች በመምጣቷ በሀገሪቱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሻሻለው የኪዮቶ ስምምነት (RKC,1999) ህጋዊ ማዕቀፍ መሰረት ይህን የትራንሸፐመንት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በኢትዮጵያ ትራንሸፐመንት ለሚደርጉ ዕቃዎች የቢዝነስ አካባቢውን ምቹ እና ተመራጭ እንዲሆን የአገልግሎት አሰጣጡን ወጥ እና ቀልጣፋ ማድረግ የሚያስችል የጉምሩክ ትራንሸፐመንት አሰራር ስርዓት ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ የአሠራር ሥርዓት በየብስ ማጓጓዣና በመጋዘን በትራንሸፐመንት ለሚጓጋዙ ዕቃ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

### 1. የአሰራር ስርዓቱ አላማ

የጉምሩክ ትራንሸፐመንት አሰራር ስርዓት ዋና አላማው ማንኛውም የትራንሸፐመንት ዕቃ ትራንሸፐ በሚያደርግበት የጉምሩክ ወደብ እንደደረሰ ወዲያውኑ ማጓጓዣውን ቀይሮ በደረሰበት አግባብ በሚቀጥለው ትራንስፖርት የመጨረሻ መዳረሻ ወደሆነው ሀገር ስለመተላለፉ የሚረጋገጥበት ቀልጣፋ የጉምሩክ የትራንሸፐመንት ስነ-ስርዓት እና ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation

## 2. ትርጓሜ

የጉምሩክ ትራንሽፐመንት ወይም ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን የማጓጓዝ ስነ-ስርዓት ማለት፡- ዕቃ በማጓጓዣ ጭኖ ወደ ጉምሩክ ወደብ ከገባ በኂላ ዕቃው ከዚያው ወደብ ተጭኖ ከአገር እንዲወጣ ሌላ ማጓጓዣ ሲቀርብ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚተላለፍበት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሲሆን በመጋዘን ላይ የሚከናወኑ ተግባራትንም ያካትታል፡፡

## 3. የጉምሩክ ትራንሽፐመንት አሰራር የህግ ማዕቀፎች

የጉምሩክ ትራንሽፐመንት አሠራር ሥርዓት ትራንሽፐ በሚያደርግበት የጉምሩክ ወደብ/ ጣቢያ የደረሰ ዕቃ ወዲያውኑ በደረሰበት አግባብ ወደ መጨረሻ መዳረሻው አገር የተላለፈ ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት፡-

1/ በአስመጭው፣ በአጓጓዡ፣ ወይም በጉምሩክ ስነ-ስርዓት አስፈፃሚው ጥያቄ የትራንሽፐመንት ዕቃ ከአንድ ማጓጓዣ ወደ ሌላ ማጓጓዣ በመቀየር ሊጓጓዝ የሚችል መሆኑ፤

2/ ማንኛውም ተፈላጊ ዝርዝሮችን የያዘ የንግድ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ እንደ ዕቃ ዲክለራሲዮን ተቆጥሮ ለትራንሽፐመንት ስነ-ስርዓት ተቀባይነት የሚኖረው መሆኑ፤

3/ ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝን ዕቃ ከአገር በሚወጣ ጊዜ ለመለየትና ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነትን ወዲያውኑ ለማስቆም የሚያስችል የጥንቃቄ እርምጃ ዕቃው በደረሰበት ወቅት መውሰድ የሚችል መሆኑ፤

4/ ኮሚሽኑ ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝ ዕቃ ከአገር የሚወጣበትን በቂ የሆነ የጊዜ ገደብ የሚወስን መሆኑ፤

5/ መጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የማይከፈልበት መሆኑ፣

6/ በህግ የተከለከሉ ዕቃዎችን መጓጓዣን በመቀየር እንዲጓጓዙ ማድረግ አለመቻሉ፤

7/ የትራንስሽፐመንት ዕቃዎችን ሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋል የማይፈቀድ ሲሆን፤ በልዩ ሁኔታ ሀገር ውስጥ ለመጠቀም ከተፈለገ በኮሚሽኑ መፈቀድና የጉምሩክ ህግን በመከተል ተገቢው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት እንዲፈጸምበት ሊደረግ ይችላል፡፡

No.1
Ethiopia Customs Comm...
Records Documentation

## 4. የስርዓቱ ተጠቃሚዎች

1/ አጓጓዥ ድርጅቶች፣

2/ የመጋዘን ኦፕሬተሮች፣

3/ ዕቃ አስተላላፊዎች፣

4/ አስመጪዎች፣ ላኪዎች

## 5. ለጉምሩክ የትራንሽፕመንት ስራ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የዕቃ አስተላላፊነት ፈቃድ ያለው፤

2/ የአጓጓዥነት የስራ ፍቃድ

3/ የንግድ ስራ ፍቃድ፤

4/ የጉምሩክ መጋዘን ፍቃድ፤

5/ ከኮሚሽኑ ሲስተም ጋር እንተርፌስ የተደረገ የመረጃ ቴክኖሎጂ፤

6/ ዋስትና ማቅረብ፤

## 6. የጉምሩክ ትራንሽፕመንት ስነ-ስርዓት አፈጻጸም ሂደቶች

### 1/ ትርጉም

ማጓጓዣ በመቀየር የሚተላለፍ ዕቃ አገር ውስጥ ከደረሰ በኃላ በሌላ ማጓጓዣ ጭኖ ከሀገር እንዲወጣ በተፈቀደው የጉምሩክ ክልል ወይም ወደብ ሲደርስ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ ወደ መጨረሻ መዳረሻ ወደ ሆነው ሀገር የሚተላለፍበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማለት ነው፡፡

### 2/ ቅድመ ሁኔታዎች

(ሀ) የትራንሽፕመንት ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ፣

(ለ) ማጓጓዣ በመቀየር የሚተላለፈው ዕቃ የተጠቃለለ ካርጎ ማንፌስት (Cargo manifest)፤

Ethiopia Customs Co...
Records Documentation

(ሐ) ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዙ ዕቃዎች ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው ሲተላለፉ አዲስ የተጠቃለለ የማስጫኛ ሰነድ ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስጫኛ የሚሄድበት መድረሻ ቦታውን የሚገልፅ ሰነድ( House way bill )

(መ) የአየር ክልል ወይም የደረቅ ወደብ ተቆጣጣሪ ሪፖርት፤

## 3/ ዝርዝር ተግባር አፈፃፀም ደረጃዎች

### ደረጃ-1

### (ሀ) የተግባር መግለጫ

ለትራንሽፕመንት ስነ-ስርዓት እንደ ዕቃ ዲክለራሲዮን የሚያገለግሉ ሰነዶችን (የኮመርሽያል እና የትራንስፖርት ሰነዶችን) በማቅረብ ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን የማጓጓዝ ስራ መከናወን አለበት።

### (ለ) አስፈላጊነት

የትራንሽመንት ስነ-ስርዓቱን ለማከናወን የዕቃ ዲክለሬሽን መሙላት ሳይጠበቅ በኮመርሻል እና የትራንስፖርት ሰነዶችን በሲስተም በመላክ አሠራሩን ለማቀላጠፍ እና የጉምሩክ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

### (ሐ) ቅድመ-ሁኔታ

በሲስተም የቀረበ የትራንሽፕመንት ፈቃድ ጥያቄ/ማመልከቻ ሰነድ መቅረብ አለበት።

### (መ) የተግባር አፈፃፀም ቅደም ተከተል


i. የትራንሽመንት ዕቃዎችን ከሌሎች የገቢ እና ወጪ ዕቃዎች ሳይቀላቀሉ ማጓጓዣ ቀይረው ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው ለማስተላለፍ የትራንሽፕመንት ፈቃድ

II. የትራንሽፕመንት ዕቃውን ወደብ እንደደረሰ ከሌሎች ዕቃዎች በመለየት ማጓጓዣ ቀይሮ ወደ መጨረሻ መዳረሻ ሀገር እስከሚተላለፍ በተወሰነለት የማከማቻ ቦታ ተለይቶ እንዲቆይ ማድረግ፤

III. ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር በተዘረጋው ሲስተም አሟልቶ መላክ፣

Ethiopia ... Recodes Documentation

## (ሠ) ስዕላዊ መግለጫ




### (ረ) ፈፃሚ

የትራንሽፐመንት አጀንቲ/አጓጓዥ ድርጅቱ

### (ሰ) የሚከናወንበት ጊዜ

በማንኛውም የስራ ሰዓት

### (ሸ) የሚወስደው ጊዜ

በፈቃድ ጠያቂው የሚወሰን ይሆናል

Ethiopia Customs Commission
Recodes_Documentation

## ደረጃ- 2

### (ሀ) የተግባር መግለጫ

የትራንሽፐመንት ካርጎ ጭነቶችን በአጓጓዡ በሚቀርብ ሰነድ መሰረት ትክክለኛነታቸውን የማረጋገጥ እና የቁጥጥር ስራ ማከናወን

### (ለ) አስፈላጊነት

የትራንሽመንት ካርጎ ጭነቶች ትራንሽፐ ወደ ሚያደርጉበት ወደብ/የጉምሩክ ጣቢያ ከደረሱ ጀምሮ ማጓጓዣ ቀይረው ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው እስከሚተላለፉ ድረስ ተገቢ የሆነ የጉምሩክ ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

### (ሐ) ቅድመ -ሁኔታ

የተጠቃለለ ካርጎ ማኒፌስት (የተጠቃለለ እና ለዕያንዳንዱ ዕቃ የተዘገጀ የመስጫኛ ሰነድ)

### (መ) የተግባር አፈፃፀም ቅ/ተከተል


I. የትራንሽመንት ካርጎ ጭነቶች ሰነዶችን ከአጓጓዡ መረከብና መረጃ መያዝ

II. የትራንሽመንት ካርጎ ጭነቶች እንደደረሱ የትራንሽመንት ዕቃዎችን በቀረበው ሰነድ አግባብ ከሌሎች የገቢ ካርጎ ጭነቶች ጋር ሳይቀላቀሉ ማጓጓዣ ቀይረው ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው እስከሚተላለፉ የሚቆዩበት ስፍራ/ የተወሰነላቸው ቦታ መግባታቸውን ማረጋገጥ እና መቆጣጠር

III. የትራንሽፐመንት ካርጎ ጭነቶችን ወደ መጨረሻ መዳረሻቸው ወደ ሆነው ሀገር ለመተላለፍ በአጓጓዡ በኩል ተዘጋጅቶ በቀረበው የተጠቃለለ ካርጎ ማኒፌስት (የተጠቃለለ እና ለዕያንዳንዱ ዕቃ የተዘገጀ የመስጫኛ ሰድ) መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation

## (ሠ) ስዕላዊ መግለጫ




(ረ) ፈፃሚ

የጉምሩክ ኦፊሰር

(ሰ) የሚከናወንበት ጊዜ

በማንኛውም 24/7 ሰዓት

(ሸ) የሚወስደው ጊዜ

በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት

## ደረጃ--3

### (ሀ) የተግባር መግለጫ

ለትራንሽፐመንት ስነ-ስርዓት እንዲከናወን ከአጓጓዡ በሲስተም በቀረበ ማመልከቻ መሰረት አረጋግጦ ትራንሽፐመንቱን የመፍቀድ ስራ ማከናወን

### (ለ) አስፈላጊነት

የትራንሽመንት ስነ-ስርዓቱን ለማከናወን የሚቀርቡ ሰነዶችን የማረጋገጥ እና የቫሊዴሽን ስራ መስራት አስፈላጊ በመሆኑ

### (ሐ). ቅድመ-ሁኔታ

የትራንሽፐመንት ፈቃድ ማመልከቻ

### (መ) የተግባር አፈፃፀም ቅ/ተከተል

I. በሲስተም የተላከውን የትራንሽፐመንት ፈቃድ ጥያቄ/ ማመልከቻ መረከብ

II. የቀረበውን ማመልከቻ አግባብነቱን አረጋግጦ የትራንሽፐመንት ስራውን መፍቀድ፣

III. በተዘረጋው የጉምሩክ ሲስተም የተላኩ ዶክመንቶችን/ ተሟልተው ስለመላካቸው ማረጋገጥ፣


IV. የትራንሽፐመንት ስራውን ለማከናወን አግባብነት ያለው ዋስትና መያዙን ማረጋገጥ፣

V. ትራንሽፐመንት ዕቃውን ለማስተላለፍ ተዘጋጅተው የቀረቡ ሰነዶችን ማረጋገጥ፣

VI. በተዘረጋው የጉምሩክ ሲስተም የጉምሩክ ትራንሽፐመንት ስነ-ስርዓት የተፈፀመባቸው ሰነዶችን የመዝጋት እና የሪኮንስሌሽን ስራ መስራት፣

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation

## (ሠ) ስዕላዊ መግለጫ




(ረ) ፈፃሚ

የጉምሩክ ኦፊሰር

## (ሰ) አፈፃፀሙ የሚከናወንበት ጊዜ

በማንኛውም የስራ ሰዓት

## (ሸ) የሚወሰደው ጊዜ

በስራ ሂደቱ ስታንዳርድ መሰረት

ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation

(ቀ) የጊዜ አጠቃቀም ማጠቃለያ

| ደረጃ | ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 | የትራንሽፐመንት ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር በሲስተም ማቅረብ | ተጠቃሚ/አጓጓዥ የድርጅቱ ወይም ወኪል | በተጠቃሚው የሚወሰን ይሆናል |
| ደረጃ 2 | የትራንሽፐመንት ካርጎ ጭነቶችን ወደብ በደረሱበት አግባብ ስለመተላለፋቸው በአካል ማረጋገጥ | የአየር ክልል ወይም የደረቅ ወደብ ተቆጣጣሪ ኦፊሰር | 24/7 |
| ደረጃ 3 | በተዘረጋው የጉምሩክ ሲስተም የቀረቡ ሰነዶችን የማረጋገጥ እና የሪኮንስሌሽን ስራ የመስራት | የጉምሩክ ኦፊሰር(ትራንዚት እና መጋዘን) | በስራ ሂደቱ ስታንዳርድ መሰረት |

Ethiopia Customs Commission
Recodes Documentation